# ወደ ኋላ እንመለስ

## ጠቃሚ ምክሩን ይማሩ

- **የሚሸውዱ ቃላትን ያስተውሉ፡** ልጅዎ ቃላት ጠፍቶት ሲቸገር/ስትቸገር፣ አስቡ፡ ይሄ ቃል ወደ ፊትም ልጇ ሊያጋጥመው/ሊያጋጥማት የሚችል ነው?
- **ጠብቁ እና አሞግሱ፡** ትዕግስት ይኑርዎት። አንዳንዴ አንባቢዎች ትንሽ ጊዜ ብቻ ነው የሚፈልጉት። ልጅዎን ለማሰልጠን ጥያቄዎችን ይጠቀሙ እንዲሁም ፊደላትን እንዲመለከቱ ያስታውሷቸው።
- **ወደ ኋላ ተመለሱ እና ከአገላለፅ ጋር በድጋሚ ያንብቡት፡** ልጅዎ ሙሉውን አርፍተነገር ወይም ሁለት ወይም ሦስት አረፍተ ነገር በድጋሚ እንዲያነብ/እንድታነብ መጠየቅ ትችላላችሁ።

**ይሄ ጠቃሚ ምክር ለምን አስፈለገ?**

ከአገላለፅ ጋር *በጥራት* ወይም *በትክክል* ማንበብ በጣም ጠቃሚ የንባብ ክህሎት ነው። ልጅዎ የሚሸውድ ቃልን ካወቀ/ች በኋላ በድጋሚ ማንበብ በጥራት የማንበብ ክህሎትን መለማመጃ በጣም ጥሩ መንገድ ነው።

## ልጅዎን ይጠይቁ

*ትንናንሽ ልጆች፡*

- ጣትህን/ሽን በመጠቀም እያንዳንዱን ድምፀት ማንበብ ትችላለህ/ትችያለሽ?
- ትችላለህ/ትችያለሽ! ደጋግመህ/ሽ ሞክር/ሪ!
- በሚሸውድው ቃል ውስጥ የምታውቀው/ቂው የቃል ክፍል አለ?

*ትልልቅ ልጆች፡*

- እየተናገርከው/ሽው ያለው ቃል ከሚታየው ፊደላት እና ድምፆች ጋር አንድ ነው?
- ይሄንን ቃል አውጥተህ/ሽ ሀረግ ውስጥ ዙሪያውን ካሉት ቃላት ጋር ማስገባት ትችላለህ/ትችያለሽ?

## አዝናኝ ልምምድ

ቀጣይ ጊዜ ፊልም ሲያዩ፣ የንግግሩን ፅሁፍ ማሳያ አብሩት። በየመሀሉ እያቆማችሁ ልጃችሁ ቴሌቪዥን ላይ የሚታየውን የንግግር ፅሁፍ ሁለት ጊዜ እንዲያነብ/እንድታነብ ያድርጉ፣ በእያንዳንዱ ጊዜ በሚችለው/በምትችለው ጥራት ለማንበብ ይ/ትሞክር። ከዛም ቪዲዮውን አጫውቱ እና በቪድዮው ላይ ያሉት ሰዎች ቃላቱን እንዴት እንደሚናገሯቸው አድምጡ።